# የጥፋት መልዕክተኛ

የጠነጠነው ሴራ ከሸፎበት
ተከናንቦ የኃፍረት ማቅ
ከተራራው ጫፍ ተቀምጦ
በሃሳብ ባሕር ሲዋዥቅ
ምን ይሻላል ብሎ ሲቆዝም
ሌላ ተንኮል ሲያውጠነጥን
የአለቆቹን ትእዛዝ ሊፈጽም
የሕዝብን ትግል ሊያዳፍን
የሁሉን አመኔታን ለማግኘት
ቃሊቲ በእስር የቆየበትን
እያስታወሰ ፈገግ ሲል
ተደብቆ ቤቱ የሚያድርበትን
እስረኛውን ለመከፋፈል
ቀን ከሌሊት ያሴረውን
አንዱን በገንዘብ ሲሞክር
ሌላው በሥልጣን ሲያባብል
የሚችለውን ሲያስፈራራ
ያልቻለውን አክራሪ ሲል
ከነአንዳርጋቸው ሲላላክ
ሲያበጣብጥ ድጋፍ ድርጅቶችን
ቅንጅት ቅንጅት ሆኖ እንዳይቀጥል
የጥፋት መሰረቱን ሲጥል
ኸረ ስንቱ ተቆጥሮ
የብርሃኑ ነጋ ጉድ ተዘርዝሮ
የሚያልቅ አይደለም ወገኖቼ
ታሪክ ይፍረደው ውሎ አድሮ::
የሥልጣን ስግብግብነቱ
የመዋሸት የመቀላመዱ
በማምታታት ችሎታው
ሊከፋፍለው አንዱን ካንዱ
ከወያኔ የተማረውን
አስቀያሚ የዘረኝነት ልምዱ::
ባሻንጉሊቱ ሲጫወት
እርሱ ያላትን እንድትፈጽም
ማንነትዋ ሳይታወቅ
አምጥቶ አስቀምጦ ከየትም
መሪ እንድትሆን ሲያስደርግ
የጠረጠረ የነቃ አልነበረም::
ሁሉም በቅን ልቦና በማሰብ
መስማማቱን ሲገልጽ በውል
የሰላም ትግል አብቅቷል
የአንዳርጋቸውን "ጦር" እንከተል ሲል
ለካስ አጅሬ ሌላ አስቧል
የጥፋት ወጥመዱን ዘርግቷል::
ሰውን ማመን ....ቀብሮ አሉ
አበው በተረት ምሳሌ ሲነግሩን
የዋኅነታችን በጣም ጎዳን
ከባቶቻችን ተረት ተማርን
የብርሃኑ ነጋን አይነት ከሃዲ
ሳናውቅ ለውድቀት መከተላችን
ዓላማው ከእኛ የተለየ
ከጠላት ሰፈር የወገነ
የጥፋት መልዕክተኛ መሆኑን::

ኃይለ ልዑል ግርማ
ዋሽንግተን ዲሲ